# ለዘውጌዎች ልምጭ

ኢትዮጵያን ሰባኪ ፣ የአነግ ደላላ
የበግ ለምድ ፣ ለባሽ ፣ የዱር አውሬ ፣ ተኩላ
የዳውድ ፣ የጀዋር ፣ ግልገል ውርንጭላ
ሃሳዊ መሲሁ ፣ ተክሎ ፣ ሁለት ባላ
መግደል ፣ መሸነፍ ነው ፣ የሚለን ቱልቱላ
ጦርነት በእስክንድር ፣ ገና ዓመት ፣ ሳይሞላ
ማንነቱ ታየ ፣ መደመር ሲሰላ ።

እግሩን የዘረጋ ፣ ሳይቀመጥ ገና
ሲባል የሰማትን ፣ ወግ አይቀርምና
ሞግታችሁ እርቱኝ ፣ በሃሳብ ልዕልና!
የማይነጋ መስሎት ፣ ያለን ትላንትና
አደባባይ ሳትቆም ፣ ከቤት ፣ ሳለች ገና
የማይቆረጠም ፣ ከብረት የፀና
ልቆ የተገኘው ፣ በሃሳብ ልዕልና
ፀሃይ ላይ ፣ አሰጣት ፣ ተጋልጣ ገመና
አልበገር ብሏል ፣ ሳተናው ባፈና
እነ ጎጥ ፣ አምላኩን ፣ ቁጭ አድርጎ ፣ ያሸና
እስክንድር ፣ ይባላል ፣ የኢትዮጲስ ጀግና ።

የጠባቦች ካህን ፣ የዘውጌ ቆራቢ
መንጋው ተጠራቅሞ ፣ ከሚኒሊክ ግቢ
የትላንት ኮሎኔል ፣ የኢንሳው ፣ ጆሮ ጠቢ
አልጨበጥ ያለው ፣ ልክ ፣ እንደ ሰላቢ
እንቅልፉን ቢነሳው ፣ ቢሆን አሳሳቢ
ላኩሲዋ እመቤት ፣ ቢሳል ለቁልቢ
ባንድ እስክንድር ፣ ብቻ ፣ እራቀው ውቃቢ ።

በስክንድር ማንነት ፣ የሚደነግጠው
ስሙ ሲጠራበት ፣ የሚቁነጠነጠው
አስሬ ፣ ሽንት ቤት ፣ ሄዶ የሚያምጠው
ሃሳቡን ለማፈን ፣ የሚንፈራገጠው
ጭንብሉ ወለቀ ፣ ዛሬ ፣ ምን ይዋጠው ?

ከሚሊዮን አብይ ፣ እስክንድር በለጠ
የኦነጉ አብይ ፣ ዛሬ ፣ አይኑ ፈጠጠ
የማይቀረው እውነት ፣ ሃቁ ተጋለጠ
የጎጥ ፖለቲካው ፣ ወረደ ዘቀጠ ።

ላስመሳዮች ትርክት ፣ ጨምላቃ ፣ እንደ ርያ
ለዘውጌዎች ልምጭ ፣ ለአብይ ፣ ማስፈራሪያ
የአንድነታችን ፣ ቃል ኪዳን ፣ ማሰሪያ
እስክንድር ነው ፣ ለኛ ፣ የህዝባችን መኩሪያ ።

ታዛቢው

June 7, 2019